# ለቅሶ ሳቅ - ሳቅ ለቅሶ

አሥራደው (ከፈረንሳይ)




አቅቶን መለወጥ ለቅሶን በደስታ፤
ሃዘን ጠል አልብሶን ሳቅ ደርቦ ኩታ፤
ያንዱን ቤት ገንብቶ የሌላውን ሲያፈርስ፤
አንዱን ሳቅ አጅቦት ሌላው ከፍቶት ሲያለቅስ፤
ለቅሶ ሳቅ - ሳቅ ለቅሶ - እየደባለቀ፤
ግማሽ ጎኑ ሲያለቅስ - ግማሽ ጎኑ ሳቀ ::

የደላው ሲጨፍር ሲደንስ ሌት ተቀን ፤
ዳንኪራ ሲመታ ሲጨልጥ ውስኪውን ፤
ያጣ በትካዜ ሲጨነቅ ሲጠበብ፤
ሲቆላ ሲታመስ በችጋር በረሃብ፤
ሆነና ዘመኑ !
የማያስተዛዝን፤
ወገን በወገኑ አብዝቶ መጨክን፤
ግለኝነት ነግሶ አብሮነት ተረስቶ፤
አንዱ ጠሙን ሲያድር: ሌላው ይጨነቃል ያለመጠን በልቶ ::

እነዚህ ሲስቁ - እኒያ ያለቅሳሉ፤
እነዚያ ሲያለቅሱ - እኒህ ይስቃሉ፤
እዚህ ቤት ሲለቀስ - እዚያ ይጨፈራል፤
እዚህ ጠም ሲታደር - እዚያ ጨማው ተርፏል፤
ተወሳሰበና - ለቅሶና ሳቃችን፤
የቸገረ ሆነ - መፍቻ ውሉ ጠፋን፤
ለቅሶ ሳቅ - ሳቅ ለቅሶ - እየደባለቀ፤
ግማሽ ጎኑ ሲያለቅስ - ግማሽ ጎኑ ሳቀ፤
ሳቅና ለቅሷችን መንስኤው ለየቅል፤
ትርጉሙ ለየራሰ የማይመሳሰል የማይቀላቀል ::

ከጉራፈርዳ ወረዳ ለተፈናቀሉ ሕፃናት ማስታወሻ የተቋጨች ::

የካቲት 3 ቀን 2005 ዓ.ም. (10/02/2013)